በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት አፈፃፀም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006

አዲስ አበባ

ማውጫ ገፅ

መግቢያ.....2

የኤጀንሲው ራዕይ እና ዓላማ.....3

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር.....3

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር.....4

የኤጀንሲው የሰው ሀይል.....4

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ.....5

የኦዲቱ ዓላማ.....6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች.....6

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria).....6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ.....7

የክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ (System Description).....7

የኦዲቱ ግኝቶች.....8

- የመድሃኒት አቅርቦትን፣ ደረጃቸውን (Standard) የጠበቁ መጋዘኖች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች መገንባትን እና መድሃኒቶችንና የሕክምና መገልገያዎችን በአግባቡ ማከማቸትን በተመለከተ.....8
- የመድሃኒቶችን ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ.....12
- የተበላሹና የአገልግሎት ማብቂያቸው ያለፉ መድኃኒቶችን በአግባቡ ማስወገድን በተመለከተ.....14
- ለመድሃኒቶች ብልሽት መንስዔዎችን መለየትና እርምጃ መውሰድን በተመለከተ.....17
- የመድሃኒት ስርጭት ስርዓት ማዘጋጀትንና መድሃኒቶች ወደ ተጠቃሚዎች በአግባቡ መድረሳቸውን በተመለከተ.....17
- የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ፍላጎት ጥያቄ አቀራረብን እና በፍላጎት መሰረት ማቅረብን በተመለከተ.....18
- የመድኃኒት አያያዝ፣ አስተዛዘዝ እና አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠርን በተመለከተ.....23
- በመድሃኒት ክምችትና ስርጭት ዙሪያ ኤጀንሲው ያለውን የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት እና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ.....24

መደምደሚያዎች.....26

የማሻሻያ ሃሳቦች.....30

አባሪ 1- የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር.....33

አባሪ 2- የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች.....34

አባሪ 3- በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ ጤና ተቋማት ዝርዝር.....38

አባሪ 4- የአሰራር ሥርዓት መግለጫ.....39

- **2.1 Linear workflow for storage**.....39
- **2.2 Linear workflow for distribution from hub to health facility**.....40

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. አገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጎራ ለማሰለፍ የተቀረፀውን የስትራቴጂያዊ መድረክ ራዕይ ዕውን ለማድረግ ከተነደፉት ንዑሳን መድረኮች ውስጥ አንዱ የሆነው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መጠነ ሰፊ ርብርብ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡
2. ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ዜጋ ከመፍጠር ውጪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሁለንተናዊ ዕድገት ሊታሰብ እንደማይችል በመገንዘብ የህብረተሰቡን ጤንነት ለመጠበቅ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በሽታን በመከላከልና በመሰረተ ጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት አቋም በመውሰድ ይህንኑ እውን ለማድረግ በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች አበረታች ውጤቶች ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡
3. በሽታን የመከላከልና የህክምና አገልግሎትን በተሟላ ሁኔታ ለመስጠት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች በሚፈለገው ዓይነትና መጠን በተመጣጣኝ ዋጋ በቀጣነት ማቅረብና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ የአጠቃላይ የሕብረተሰቡን ጤንነት ለማሳደግ በተለይም አስተማማኝ የሆነ የመድሃኒትና የጤና አገልግሎት አቅርቦት ዕቅዱን ለማስፈፀም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡
4. በሀገሪቱ ዋናዋና ችግሮች ላይ ያተኮረ ጥራታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶችን በበቂ መጠን፤ በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለጤና ተቋማት ለማቅረብ በአዋጅ ቁጥር 553/2007 ዓ.ም ፋርሚድ የሚለው የበፊት ስያሜ ተቀይሮ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በሚል እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
5. ኤጀንሲው የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች አቅርቦት በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ አገር ገዝቶ የሚያቀርባቸው መድኃኒቶች ከአመታት በፊት ከ700 ሚሊዮን ብር የማይበልጥ የነበረው በአሁን ወቅት 3.5 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ በአሁኑም ወቅት ኤጀንሲው በመላው ሃገሪቱ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎችን ለማሰራጨት ይረዳው ዘንድ አስራ አንድ ቅርንጫፎችን በተለያዩ አካባቢዎች (አዲስአበባ፣ ሃዋሳ፣ ደሴ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ነቀምት፣አዳማ፣ ደምቢዶሎ፣ ድሬዳዋ፣ እና መቀሌ) በመክፈት ለመንግስትና ለግል ጤና ተቋማት መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡

የኤጀንሲው ራዕይ እና ዓላማ

ራዕይ (Vision)

6. “የሕብረተሰቡ የመድኃኒት ፍላጎት ተሟልቶና በአግባቡ ተጠቅሞ ጤንነቱ ተጠብቆ ማየት”

ዓላማ (Objective)

7. ኤጀንሲው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡-
   - የመንግስት ጤና ተቋማት ጥራታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ እንዲያቀርቡ የማስቻል፤
   - የመድኃኒት አቅርቦቱን በማጠናከርና ዘለቄታዊነቱን በማረጋገጥ የጤና አገልግሎቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ አስተዋፅኦ የማድረግ፤
   - ፈንዱ ወጪውን እንዲሸፍን ከተደረገ በኃላ ተመልሶ በማዟዟር እራሱን በማሳደግ ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች እውን ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

8. ኤጀንሲው በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-
   - በመድኃኒት ፈንድ በመጠቀም በሀገሪቱ ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮሩ ጥራታቸው የተረጋገጠ መሰረታዊ መድኃኒቶችን በበቂ መጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመንግስታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የግዥና የስርጭት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤
   - ዘመናዊ የክምችት አስተዳደር ለማስፈን የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፤
   - የክምችትና የስርጭት አውታሮችን ፍትኃዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ ያስፋፋል፣ ያጠናክራል፤
   - አግባብ ባለው አካል ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን ለመንግስት የጤና ተቋማት ያቀርባል፣ አግባብ ሆኖ ሲገኝ በበቂ መጠን ሊቀርቡ ያልቻሉ የተመረጡ መድኃኒቶችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መንግስታዊ ላልሆነና ለግል የጤና ተቋማት ያቀርባል፤
   - የማጓጓዣ ሥርዓትን በማመቻቸት መድኃኒቶችን በቀጥታ ለወረዳዎች ሆስፒታሎችና እንደአመቺነቱ ለጤና ጣቢያዎች ያደርሳል፤
   - በዘርፉ ከሚዘረጋው ስርዓት ጋር የሚጣጣም ዘመናዊ የሎጂስቲክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ይዘረጋል፤
   - የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የግዥ፣ የስርጭት፣ የማከማቸትና የማጓጓዝ ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገብራል፣ አፈፃፀሙንም ይገመግማል፤

- በሚያከናውናቸው የስራ ዘርፎች ላይ ሙያዊ የምክር አገልግሎትና ሥልጠና ይሰጣል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውን ይመራል፣ያስተባብራል፤
- ለሚሰጠው አገልግሎት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ክፍያ ያስከፍላል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
- ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር

9. ኤጀንሲው የሚመራው በቦርድ (በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር አቅራቢነት አግባብ ካላቸው የፌዴራል መንግስት አካላት በመንግስት የሚሰየሙና ከክልሎች የተውጣጡ አባላት ያሉት) ሲሆን፤ ተጠሪነቱም ለፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ነው፡፡ አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ሰባት ዳይሬክቶሬቶች፣ አስራ አንድ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣ አንድ ቅርንጫፍ አስተባባሪ ቢሮ እና አንድ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ በኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ይገኛሉ፡፡ (አባሪ 1)

የኤጀንሲው የሰው ሀይል

10. በ2005 ዓ.ም በኤጀንሲው እና በቅርንጫፎች የሚገኘው የሰው ሀይል ብዛት በአጠቃላይ 949 ሲሆን ዝርዝር መረጃው እንደሚከተለው ቀርቧል-

ትምህርት ደረጃ	ወንድ (%)		ሴት(%)		ድምር	በመቶኛ (%)
በማስትሬት	9	(0.95)	0	-	9	(0.95)
በድግሪ	165	(17.4)	44	(4.6)	209	(22)
በዲፕሎማ	153	(16.1)	86	(9.1)	239	(25.2)
በቴክኒክና ሙያ	39	(4.1)	23	(2.4)	62	(6.5)
ከ9-12ኛ	167	(17.6)	45	(4.7)	212	(22.3)
ከ1-8ኛ	139	(14.6)	31	(3.3)	170	(17.9)
ማንበብና መፃፍ	15	(1.6)	1	(0.1)	16	(1.7)
ሌሎችና ሰርተፍኬት	12	(1.3)	20	(2.1)	32	(3.4)
ድምር	699	(73.7)	250	(26.3)	949	(100)

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

11.ከ 2002 እስከ 2005ዓ.ም ያለው የኤጀንሲው የተመደበ በጀትና አጠቃቀም እንደሚከተለው ቀርቧል-

ተ.ቁ	በጀት ዓመት /ዓ.ም/	የተመደበ በጀት /በብር/ ('000,000,000)			ጥቅም ላይ የዋለ በጀት /በብር/ ('000,000,000)			አጠቃቀም /በመቶኛ/
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር	መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
1	2002	0.055	1.858 ከዚህ ዉስጥ ብር 1.146 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	1.914	0.049	1.7	1.75	92
2	2003	0.371 ከዚህ ዉስጥ ብር 0.286 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	3.619 ከዚህ ዉስጥ ብር 1.784 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	3.99	0.209	3.586	3.796	95.13
3	2004	0.725 ከዚህ ዉስጥ ብር 0.653 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	5.2. ከዚህ ዉስጥ ብር 3.1 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	5.925	0.499	4.971	5.471	92.34
4	2005	0.55	6 ከዚህ ዉስጥ ብር 3.6 የጤና ፐሮግራም ነዉ፡፡	6.552	0.503	5.7	6.203	94

የኦዲቱ ዓላማ

12.የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችትና ስርጭት ሂደት፣ አስፈላጊ መድሃኒቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ እያደረገና ለዜጎች ጤንነት መሻሻል አወንታዊ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ በአፈፃፀም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን መስጠት ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

13.ከላይ የተመለከተውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፤

1. ደረጃቸውን የጠበቁ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያ ማከማቻዎች መስፋፋታቸውንና ዘመናዊ የክምችትና የአወጋገድ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
2. ደረጃቸውን የጠበቁ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያ የስርጭት አውታሮች መስፋፋታቸውንና በወቅቱ ለጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
3. የመድኃኒት ክምችት እና ስርጭት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

14.ለኦዲቱ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት መመሪያ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አለም አቀፍ የመድሃኒት አያያዝ ህጎችና ደንቦች እና ቃለ መጠይቆችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ለተመረጡት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 58 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ መስፈርቶቹም ለኤጀንሲው ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15.የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 እስከ 2006 ዓ.ም ሩብ አመት ሲሆን፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት አፈፃፀም ላይ የተከሰቱ አበይት ክፍተቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /Ethiopian Performance Audit Standards/ መሰረት ሲሆን፣ ለክዋኔ ኦዲቱ በተዘጋጁ የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነው እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሰራተኞች ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡

ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ ከግዥና ትንበያ ዳይሬክቶሬት ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የመረጃ ክለሳ በማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም በክልል እና በፌደራል የሚገኙ እና በናሙና ከተመረጡ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የጅማ፣ የነቀምት፣ የባህርዳር የደሴ እና አዲስአበባ ቅርንጫፍ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም በናሙና ከተመረጡ የመንግስት ጤና ተቋማት፤ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የጋምቤላ ሆስፒታል፣ የነቀምቴ ሪፈራል ሆስፒታል፣ የፈለገ-ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል፣ የደሴ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የአስር ጤና ጣቢያ የመድሃኒት መጋዘን ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና መረጃዎችን በመሰብሰብ ተተንትነዋል፡፡ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ ጤና ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

የክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ (System Description)

16.ደረጃቸውን የጠበቁ የመድኃኒት ማከማቻዎችና የስርጭት አውታሮችን በማጠናከርና በማስፋፋት ተመጣጣኝ መድኃኒቶችን በክምችት በመያዝና ወትሮ ዝግጁነትን በማረጋገጥ በወቅቱ ለጤና ተቋማት እንዲቀርቡ ማድረግ፣ በክምችትና ሥርጭት የሚታየውን ብክነቶች በመቀነስ ህብረተሰቡ ጥራት ያላቸው መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ፣ አግባብ ያለው የመድኃኒት አጠቃቀምን በጤና ባለሙያዎችና በተጠቃሚዎች ዘንድ በማስፈን የኅብረተሰቡን ጤንነት ማጎልበት፣ በክምችትና ስርጭት ዳይሬክቶሬት የሚከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች ሲሆኑ፤ የዳይሬክቶሬቱ አጠቃላይ የመድሃኒት ክምችትና ስርጭት የሥራ ፍሰት መግለጫ በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

የመድሃኒት አቅርቦትን፣ ደረጃቸውን (Standard) የጠበቁ መጋዘኖች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች መገንባትን እና መድሃኒቶችንና የሕክምና መገልገያዎችን በአግባቡ ማከማቸትን በተመለከተ

የመድሃኒት አቅርቦትና ክትትልን በተመለከተ

17. ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና እና ያልተቋረጠ አቅርቦት የሚኖርበት ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የመድኃኒት ብክነት እና እጥረት እንዳይደርስ ለመከላከል የተጠናከረ የመድኃኒት ክምችትና ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የመንግስት ሕክምና መስጫ ተቋማት እንደታየው፤ የመድሃኒት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም፣ አሁንም የአቅርቦት መቆራረጥና ክፍተት መኖሩ ታውቋል፡፡ በተለይ የኬሚካሎችና ላብራቶሪ ሪኤጀንቶች (Chemicals and lab-reagents) አቅርቦት ከፍተኛ እጥረት አለበት፡፡ በተጨማሪም በናሙና የታዩት ሁሉም (17) ጤና ተቋማት ኤጀንሲው የተጠየቁትን መድሃኒቶች ሙሉ ለሙሉ ማቅረብ እንዳልቻ የገለፁ ሲሆን፤ ከታዩ ጤና ተቋማትም በፈለገ-ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል በቀን 1/21/2006 ዓ.ም በተደረገ ጉብኝት በሆስፒታሉ መድሃኒት ማከማቻ መጋዘን 42 አይነት አስፈላጊ መድሃኒቶች ምንም ክምችት አልነበራቸውም፡፡

19. ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ በናሙና ከታዩት 17 መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት ለመረዳት እንደተቻለው በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችት ዙሪያ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የሚያደርጉት ክትትልና ቁጥጥር ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ የሌለው እንደሆነ ታይቷል፡፡

20. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ከላይ ስለተነሱት ጉዳዮች በሰጡት ምላሽ፣ አብዛኛዎቹ ኬሚካሎችና ላብራቶሪ ሪኤጀንቶች ሲመረቱ ውሱን በሆነ የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ብቻ ጥቅም እንዲሰጡ ስለሆነ በተፈለገው መጠን ለጤና ተቋማት ለማሰራጨት እንዳልተቻለ እና በመድሃኒቶች አቅርቦት ዙሪያም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ መሻሻሎች ቢኖርም እጥረቱ እንዳለ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በመንግስት ጤና ተቋማት ላይ በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችት ዙሪያ ክትትልና ጉብኝቶችን የማድረግ ስርዓቱ ቢኖርም፣ ክፍተቶች

እንዳሉና ለዚህም ዋናው ምክንያት ለክትትልና ቁጥጥር ከዋና መ/ቤት ለቅርንጫፎች የሚመደበው በጀት ከረጂ ድርጅቶች የሚገኝ በመሆኑ በጀቱ በተፈለገው ጊዜ እንደማይለቀቅ አብራርተዋል፡፡

21.የመድሃኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች አቅርቦት ላይ መቆራረጥ መኖሩ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን ከግል አቅራቢዎች እንዲገዙና በመድሃኒት ግዥ ሥራ እንዲጠመዱ ምክንያት ሲሆን፤ በመንግስት ጤና ተቋማት የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችትን በተመለከተ በኤጀንሲው የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር የተጠናከረና ወጥ የጊዜ ሰሌዳ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ኤጀንሲው በተቋማቱ ያሉትን ችግሮች ለይቶ የማሻሻያ ሃሳቦች እንዳይሰጥና በጤና ተቋማት ተገቢ ያልሆነ የመድሃኒት ክምችት እንዲኖር አድርጓል፡፡

<u>**የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖችን በተመለከተ**</u>

22.ለመድኃኒት አያያዝ አመቺ የሆኑና ለየአካባቢው የአየር ጠባይ የሚስማሙና የተደራጁ ዘመናዊ መጋዘኖች በሁሉም ክልሎች ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ የመረከቢያ፣ የማከማቻና የማስረከቢያ መጋዘኖች የተለያዩ መሆን አለባቸዉ፡፡

23.ኤጀንሲው አስራ አንድ የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ያሉት ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ አራት በኦሮሚያ፣ ሶስት በአማራ፣ አንድ በደቡብ፣ አንድ በትግራይ፣ አንድ በድሬዳዋ እንዲሁም አንድ በአዲስ አበባ ሲገኙ የተቀሩት ክልሎች፤ ማለትም ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ እና አፋር የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘን የላቸውም፡፡ በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው ከተጎበኙ 17 የመንግስት ጤና ተቋማት መካከል የአስሩ ተቋማት መድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ዘመናዊና ለአካባቢው አየር ጠባይ ተስማሚ ተደርገው የተሰሩ መጋዘኖች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡ ከዚህም በላይ፤ በናሙና የታዩት የጅማ፣ የነቀምቴ፣ የባህርዳር እና የደሴ ቅርንጫፎች የማስረከቢያና የመረከቢያ ቦታ የተለያዩ ባለመሆናቸው በአንድ ቦታ ተደራራቢ ስራዎች እንዲከናወኑ አድርጓል፡፡ በተለይም በጅማ እና ደሴ ቅርንጫፎች ከፍተኛ የመድሃኒት ማከማቻ የቦታ ጥበት ታይቷል፡፡

24.የኤጀንሲው ኃላፊዎች በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ ችግሩን ለመቅረፍ 17 ደረጃቸውን የጠበቁ አዳዲስ መጋዘኖች ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት ለመድሃኒት ክምችት ተስማሚ የሆነ መጋዘኖች እንዲኖሯቸው የማግባባት ስራዎች እንደሚሰሩና ኤጀንሲው ለዚህ ኃላፊነት እንደማይወስድ ጠቁመዋል፡፡

25.በሁሉም ክልሎች የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ባለመኖራቸውና ያሉትም መጋዘኖች በዘመናዊ መልክ ባለመደራጀታቸው እንደ ደሴ ባሉት የኤጀንሲው ቅርንጫፎች መድሃኒቶች ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከመጋዘን ውጪ እንዲከማቹና ችግሩ ሳይፈታ እንዲቀጥል አድርጎታል፡፡

26.ለመረከቢያ፣ ለማከማቻና ለማስረከቢያ መጋዘኖች አገልግሎት የሚውሉ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች (የሙቀት መለኪያዎች፣ ፎርክሊፍት፣ ጋሪ፣ ፓሌት፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶች ወዘተ) መሟላት አለባቸው፡፡

27.በናሙና ከታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች አብዛኛዎቹ ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች አልተሟሉላቸውም፡፡ ችግሩ በተመሳሳይ ሁኔታ በኦዲቱ በታዩ የኤጀንሲ ቅርንጫፍ መጋዘኖች ላይም ታይቷል፡፡ በኦዲቱ እንደታየው በጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና በጳውሎስ ሆስፒታል ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች የሌሏቸው ሲሆን፤ በጅማ፣ ደሴና ባህርዳር የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ግብዓቶቹ ሙሉ ለሙሉ አልተሟሉም፡፡ በኦዲቱ በታዩ ጤና ተቋማትና የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች የአስፈላጊ ቁሳቁሶች አቅርቦት ሁኔታ በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	የጤና ተቋሙ/ የቅርንጫፉ ስም	የሚገኙበት ክልል	የግብዓት አይነት				
			ቴርሞ-ሜትር	አየር ማቀዝቀዣ	ቀዝቃዛ ሰንሰለት ክፍል/በቂ ፍሪጅ	እሳት ማጥፊያ	ፎርክሊፍት
1.	ጅማ ዩ/ስ/ ሆስፒታል	ኦሮሚያ	×	×	×	×	*
2.	ሰርቦ ጤና ጣቢያ		⌞	×	×	×	*
3.	አጋሮ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
4.	ነቀምቴ ሪ/ሆስፒታል		×	×	×	×	*
5.	ጉቴ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
6.	ኡኬ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
7.	ጅማ ቅርንጫፍ		×	×	×	×	⌞
8.	ነቀምቴ ቅርንጫፍ		⌞	⌞	⌞	⌞	⌞
9.	ጋምቤላ ሆስፒታል	ጋምቤላ	×	⌞	×	×	*
10.	ጋምቤላ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
11.	ቦንጋ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
12.	ፈለገሂዎት ሪ/ሆስፒታል	አማራ	×	×	×	×	*
13.	መራዊ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
14.	ወረታ ጤና ጣቢያ		⌞	⌞	×	×	*
15.	ደሴ ሪ/ሆስፒታል		×	×	×	×	*
16.	ጢጣ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
17.	ኮምቦልቻ ጤና ጣቢያ		×	×	×	×	*
18.	ባህርዳር ቅርንጫፍ		⌞	×	⌞	⌞	⌞

19.	ደሴ ቅርንጫፍ		×	×	˪	˪	×
20.	ጳውሎስ ሆስፒታል	አዲስ አበባ	×	×	×	×	*
21.	ጥቁር አንበሳ ሪ/ሆስፒታል		×	×	×	×	*
22.	አዲስአበባ ቅርንጫፍ		×	×	×	˪	×

ሰንጠረዥ 1- አስፈላጊ ቁሳቁሶች በጤና ተቋማት መድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች

<u>ማውጫ</u>

×- ግብዓቱ አልተሟላም

˪- ግብዓቱ ተሟልቷል

*- ግብዓቱ ለተቋሙ አስፈላጊ አይደለም

28. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለጉዳዩ እንዳብራሩት፣ የግብዓቶቹ አለመሟላት በመድሃኒቶች ክምችት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ቢችልም፣ ጤና ተቋማት ግብዓቶቹን እንዲያሟሉ ለኃላፊዎች ምክርና ግንዛቤ ከመስጠት ውጭ ለአንዳንድ ተቋማት አቅምን ባገናዘበ መልኩ የቁሳቁስ ድጋፍ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡ አዳዲስ እየተገነቡ ላሉት የኤጀንሲው መድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ግን ግብዓቶቹ እንደሚሟሉላቸው አብራርተዋል፡፡
29. ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በመንግስት ጤና ተቋማት አለመሟላታቸው ተገቢ የሆነ የመድሃኒት አከመቻቸት ስርዓትን ለመፍጠር እንቅፋት ፈጥሯል፡፡
30. ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ቁልፍ ባለው የብረት ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል መቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት ባለሙያ እጅ መሆን አለበት፡፡
31. በኦዲቱ ተመርጠው በናሙና ከታዩት 17 መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በ15 ተቋማት የመድሃኒት መጋዘኖች ውስጥ ለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የተለየ ሳጥንም ሆነ የተለየ ባለሙያ የለም፡፡ በተጨማሪም በኤጀንሲው የጅማ ቅርንጫፍ ያለው የተለየ ሳጥን ቁልፍ ተበላሽቷል፡፡
32. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በጤና ተቋማት ውስጥ ለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ማከማቻ የተለየ ቁልፍ ያለው ሳጥን የማደራጀት ስራ የተዋረድ አካላት ኃላፊነት ሲሆን፣ ይህንን ማረጋገጥ ደግሞ የተቆጣጣሪ አካላት ድርሻ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
33. ተለይተው በጥንቃቄ መቀመጥ ያለባቸው መድሃኒቶች ከሌሎች መድሃኒቶች ጋር ተቀላቅለው ያለጥንቃቄ መከማቸታቸው ተገቢና ጥንቃቄ የተሞላበት የመድሃኒት ክምችት ስርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

34.በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በመንግስታዊ የሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት የሚኖረዉ የክምችት መጠን ከሚፈለገዉ በታች ወይም በላይ እንዳይሆን ወይም በአጠቃላይ ከክምችት ጠፍቶ ችግር እንዳይፈጠር የክምችት መጠን አመላካቾች (Average monthly consumption, Minimum stock level, safety stock Level) በየደረጃዉ (በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በጤና ተቋሞች) በሥራ ላይ ማዋል አለባቸዉ፡፡

35.በናሙና ከታዩ መንግስታዊ ጤና ተቋማት መካከል በቦንጋ ፣ በጋምቤላ፣ በሉኬ፣ በጢጣ እና በጉቴ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በጥቁር አንበሳና ጳውሎስ ሆስፒታሎች የመድሃኒት መጠን አመላካቾቹ ስራ ላይ አልዋሉም፡፡

36.ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ማብራሪያ የ IPLS (Integrated pharmaceuticals logistics system) በጤና ተቋማት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ የተጀመረ ቢሆንም ባለው የግብዓት ውሱንነት ለሁሉም ጤና ጣቢያዎች በኮምፒውተር የታገዘና ክምችቶቹን የሚያሳይ የክምችት ስርዓት አለመዘርጋቱን ገልፀው በባለሙያ ተደጋጋሚ ቅይይር የስርዓቱ አፈፃፀም ላይ ክፍተቶች እንደሚፈጠሩ ገልፀዋል፡፡

37.ሆኖም የክምችት መጠን አመላካቾቹ በጤና ተቋማቱ ስራ ላይ አለማዋላቸው ተቋማቱ ያላቸውን የክምችት መጠን አውቀው፣ መድሃኒቶቹ ከማለቃቸው በፊት በወቅቱ ለማዘዝ ካለማስቻሉም በላይ ኤጀንሲውም ተቋማቱን በተገቢው መንገድ እንዳይከታተላቸው አድርጓል፡፡

የመድሃኒቶችን ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ

<u>ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል መድሃኒት ክምችትን በተመለከተ</u>

38.ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ክምችት ያላቸው ቅርንጫፎችና የጤና ተቋማት ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በማከማቻ መጋዘን የሚገኘዉን የክምችት ይዘት ዕለት ከዕለት በሚኖረዉ የመረጃ ስርዓት በመከታተል ለሚመለከተዉ አካል አስፈላጊዉ መረጃ (ከፍተኛና ዝቅተኛ ክምችት የሚታይባቸዉ፣ አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸዉ የመጠቀሚያ ዘመናቸዉ ለማብቃት የተቃረቡ ወዘተ) መተላለፍ አለበት፡፡

39.በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩት 17 መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎችን ዝርዝር ለኤጀንሲው ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ በተጨማሪም በናሙና የታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት በመጋዘናቸው ውስጥ የሚገኘዉን የመድሃኒት ክምችት ይዘት ሪፖርት የሚያደርጉበት ስርዓት የለም፡፡

40.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአሁኑ ጊዜ በኤጀንሲውና በጤና ተቋማት መካከል ያለው ጠንካራ የሪፖርት ልውውጥ ለፕሮግራም መድሃኒቶች በየሁለት ወሩ የሚቀርበው የመድሃኒት መጠየቂያና ሪፖርት ማድረጊያ ቅፅ (RRF-Report and Request Format) እንደሆነና ሪፖርቱ ከላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያካትት ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት መድሃኒቶች ሌሎች ሪፖርቶችን ወደፊት በተደራጀ ሁኔታ ለመለዋወጥ ዕቅድ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

41.ሆኖም ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ ክምችት ያላቸው ጤና ተቋማት ለኤጀንሲው ሪፖርት አለማድረጋቸው መድሃኒቶች ጥቅም ሳይሰጡ የአገልግሎት ማብቂያቸው እንዲያልፍ እና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ሳይሰጡ በክምችት እንዲቆዩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት በክምችት የሚገኙ መድሃኒቶችን ይዘት ሪፖርት አለማድረጋቸው ኤጀንሲው በተቋማቱ ያለውን የክምችት መጠን እንዳይከታተልና መረጃውን ለቀጣይ የመድሃኒት ስርጭት ዕቅድ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

<u>የመድሃኒት ቆጠራ ሪፖርትን በተመለከተ</u>

42.ማንኛዉም በኤጀንሲዉ የሚገኝ የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ክምችት ቆጠራ በበጀት ዘመኑ ማብቂያ መደረግ እና የቆጠራው ዉጤት ከሐምሌ 30 በፊት ተጠቃሎ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡ በሥራ ሂደት የተሰበሩና የተበላሹ መድኃኒቶች በየ3 ወር እና ዓመታዊ ቆጠራ ከመከናወኑ በፊት ዝርዝራቸዉን ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት በማድረግ ዉሳኔ ተሰጥቶበት በኮሚቴ እንዲወገዱ መደረግ አለበት፡፡

43.በኦዲቱ የታዩት የጅማ፣ ነቀምቴ፣ ባህርዳር፣ ደሴ እና አዲስ አበባ ያሉ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የ 2005 ዓ.ም ቆጠራ ሪፖርት አጠቃለው ለማዕከል አላቀረቡም፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ እንደታየው መንግስታዊ ጤና ተቋማት ዓመታዊ የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ ቆጠራ ሪፖርት ለኤጀንሲው እንደማይልኩና ለተሰበሩና ለተበላሹ መድሃኒቶች ቋሚና ወጥ የሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ እንደሌለ ታይቷል፡፡

44. የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ኃላፊዎች ስለቆጠራው ሪፖርት መዘግየት ተጠይቀው ቅርንጫፎች በእጃቸው ያለውን ክምችት የሚያሳይ መረጃ እንደሚልኩና መዘግየቱ የተከሰተው ብልጫና ጉድለትን ለይቶ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን የያዘ የቆጠራ ሪፖርት ለመላክ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚፈልግ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት የቆጠራ ሪፖርታቸውን ለኤጀንሲው መላክ እንደማይጠበቅባቸው አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተበላሹ መድኃኒቶችን በተመለከተ የኤጀንሲው የነቀምት ቅርንጫፍ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣

ከ5000 ብር በታች የሆኑ የመድሃኒት ብልሽቶችን እዚያው እንደሚያስወግዱ፤ ነገር ግን ቋሚ የሆነ የመድሃኒት ብልሽት ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የጅማ፣ ባህርዳር፣ ደሴና አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ኃላፊዎች ለተበላሹ መድኒቶች ቋሚ የሆነ ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ እንዳልተዘጋጀ አስረድተዋል፡፡

45. ሆኖም የቅርንጫፎች የቆጠራ ሪፖርት በጊዜው አለመቅረቡ፣ የጤና ተቋማትን የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ቆጠራ ውጤት አለማወቁ እና በሥራ ሂደት የተሰበሩና የተበላሹ መድኃኒቶች ቋሚ በሆነ የመድሃኒት የጊዜ ሰሌዳ ሪፖርት አለመደረጋቸው ኤጀንሲው እንደ አጠቃላይ በአዲስ በጀት ዓመት በእጁ ያሉትን ግብዓቶች ዝርዝር እንዳያውቅና መረጃውን ለክትትል፣ ቁጥጥር እና ለቀጣይ ዓመት ዕቅድ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

የተበላሹና የአገልግሎት ማብቂያቸው ያለፉ መድኃኒቶችን በአግባቡ ማስወገድን በተመለከተ

ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል መድሃኒት አወጋገድን በተመለከተ

46. በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አግባብ ባለው መንገድ የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

47. በኦዲቱ እንደታየው በጤና ተቋማትና በኤጀንሲው ቅርንጫፎች በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ለማይውሉ መድኃኒቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገዱ የተዘረጋ ወጥ የሆነ ስርዓት ባለመኖሩ፣ በናሙና በታዩት የኤጀንሲው ቅርንጫፎችና ጤና ተቋማት ጥቅም የማይሰጡ መድሃኒቶችና ሕክምና መገልገያዎች ጉድጓድ ተቆፍሮ እንዲቃጠሉ ይደረጋል፡፡

ምስል 1- አግባብ ያልሆነ የመድሃኒት አወጋገድ በጋምቤላ ሆስፒታል

48.ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ችግሩ መኖሩን ገልፀው ችግሩን ለመፍታት ኤጀንሲው ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ችግሩን ለመፍታት ኢንቨስትመንት ስለሚፈልግ ከኤጀንሲው ባለፈ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ርብርብ እንደሚፈልግ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

49.አግባብ ያለው የመድሃኒት አወገገድ ስርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ የሚወገዱ መድሃኒቶች በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ጉዳት እንይታወቅና ችግሩን ለመቀነስ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ አድርጓል፡፡

<u>የመድሃኒቶች ማስወገጃ የጊዜ ሰሌዳና የህክምና መሳሪያዎች ክምችትን በተመለከተ</u>

50.በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት መመሪያ እንደተቀመጠው በማዕከልና ቅርንጫፍ መጋዘኖች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በየሩብ አመቱ መጨረሻ የተቆጣጣሪው ባለስልጣን ተወካዮች ባሉበት እንዲወገዱ ተደርጎ የማስወገጃ ሰርተፊኬት (Disposal certificate) በወቅቱ እንዲቀርብ ክትትል መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ለተጠቃሚው ቀርበው ለ5 ዓመት እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው (በሚፈለገው መልኩ ለተጠቃሚው አገልግሎት የማይሰጡ) የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር ለሚመለከተው አካል እየቀረቡ እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

51.በናሙና በታዩት የነቀምት፣ የጅማ፣ የባህርዳር፣ የደሴ እና የአዲስ አበባ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶችን ለማስወገድ ቋሚ የሆነ የማስወገጃ

የጊዜ ሰሌዳ ካለመኖሩም በተጨማሪ በጋምቤላ፣ በደሴ፣ በፈለገ ህይወት ሆስፒታሎች እንዲሁም በኤጀንሲው የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ የተለያየ አይነት ያላቸው የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ጥቅም ሳይሰጡ እና በኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ሳይወገዱ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በሌላ የመድሃኒት ዓይነት ተተክተው ግልጋሎት እንዳይሰጡ የታገዱ ነገር ግን የአገልግሎት ማብቂያቸው ያላለፉ የፀረ-ኤች አይ ቪ እና የቲቢ መድሃኒቶች ከኤጀንሲው የመፍትሄ አቅጣጫ ስላልተቀመጠላቸው ጥቅም ሳይሰጡ በመራዊ ጤና ጣቢያ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

ምስል 2- ጥቅም ሳይሰጡ ተከማችተው ከሚገኙ ሕ/መገልገያዎች ደሴ ሆስፒታል

52.ስለ አወጋገድ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ኃላፊዎች ተጠይቀው እንዳብራሩት፣ የማስወገድ ሂደቱ የሚፈልገው ጊዜና ሃብት ከፍተኛ በመሆኑ በአብዛኛው በቆጠራ ወቅት በዓመት አንድ ጊዜ ለማስወገድ እንደሚሞከር እንዲሁም በቅርንጫፎች ያለው የሕክምና መገልገያዎች ዝርዝር ለኤጀንሲው ሪፖርት እንደተደረገና እንደአጠቃላይ በሃገርአቀፍ ደረጃ የሕክምና መገልገያዎች ኦዲት ለማድረግ ዕቅድ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

53.የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመወገዳቸው እንደ ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና የኤጀንሲው አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ባሉ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ የተበላሹ መድሃኒቶች ክምችት እንዲፈጠርና ለማስወገድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በቅርንጫፎችና በጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ጥቅም የማይሰጡ ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ለጉዳዩ ተገቢው

የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ መሳሪያዎቹ ወደ ሌላ ተቋም ተዘዋውረው ጥቅም ሊሰጡ የሚቻልበት እድል እንዳይፈጠር እንዲሁም ጥቅም የማይሰጡት አግባብ ባለው ሁኔታ እንዳይወገዱና የማከማቻ ቦታ ጥበት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

ለመድሃኒቶች ብልሽት መንስዔዎችን መለየትና እርምጃ መውሰድን በተመለከተ

54. የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ በማወቅ ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡
55. በኦዲቱ በታዩት አምስት የኤጀንሲው ቅርንጫፎችም ሆነ 17 የመንግስት ጤና ተቋማት በስራቸው የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ ለማወቅ ያጠኑት ጥናት የለም፡፡
56. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የተለያዩ ጥናቶች በማዕከል ደረጃ እንደተደረጉና (ለምሳሌ የBPR ጥናት) ዋናው የመድሃኒቶች ብልሽት መንስዔ በእርዳታ የሚገቡ መድሃኒቶች መሆናቸውን ጠቁመው፣ ጥናቶቹ ግን የተጠናከሩ እንዳልሆኑና በቅርንጫፍ ደረጃም ጥናቶች ቢሰሩ ጠቃሚ እንደሆነ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡
57. ለመድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ብልሽት እና ጥቅም ላይ አለመዋል እንደ መንስዔ ሊጠቀሱ የሚችሉ ጉዳዮችን የሚያሳይ ጥናት አለመደረጉ ኤጀንሲው ለመድሃኒት ብልሽት አበይት ምክንያቶችን ለይቶ ችግሩን ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ እንዳይወስድ አድርጓል፡፡

የመድሃኒት ስርጭት ስርዓት ማዘጋጀትንና መድሃኒቶች ወደ ተጠቃሚዎች በአግባቡ መድረሳቸውን በተመለከተ

<u>ወጪ የተደረጉ መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋማት መድረሳቸውን በተመለከተ</u>

58. ለጤና ተቋማት ወጪ የሚደረገው መድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ወደ ተቋማቱ ለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
59. በኦዲቱ እንደታየው ለመደበኛ የግዥ መድሃኒቶች ኤጀንሲው መድሃኒቶቹ ወደ ጤና ተቋማቱ ለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት በአዲስ ህይወት ሆስፒታል በ2002 ዓ.ም ብር 110,000፣ በአሶሳ ዞን ጤና ፅ/ቤት በ2001 ዓ.ም ብር 197,575፣ በአባይ ጤና ጣቢያ በ2003 ዓ.ም ብር 38,429፣ በባህርዳር አስተዳደር ጤና ፅ/ቤት በ2003 ዓ.ም ብር 23,436፣ በማሻ ጤና ጣቢያ በ2005 ዓ.ም ብር 46,000 እና በገንጂ ጤና ጣቢያ በ2005 ዓ.ም ብር 113,702 የሚያወጡ መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋማቱ ሳይደርሱ ሊጭበረበሩ ሲሉ ተይዘው ጉዳዩ በህግ እንዲታይ ተደርጓል፡፡

60.የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ቅርንጫፍና ማዕከል ኃላፊዎች ክፍተቱ መኖሩንና ወደፊት መድሃኒቶችን በቀጥታ ለተቋማት ማድረስ ሲጀመር ችግሩ እንደሚቃለል ገልፀዋል፡፡ በአሁኑም ወቅት ችግሩን ለማቃለል በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች መድሃኒቶችን በቀጥታ ወደ ጤና ተቋማት የማድረስ ሥራ መጀመሩን አብራርተዋል፡፡

61.ጤና ተቋማት በግዥ ለሚወሰዷቸው መደበኛ መድሃኒቶች ወደ ተቋማቱ ስለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ባለመኖሩ የመድሃኒት ማጭበርበር ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>የመድሃኒቶች ማጓጓዝ ሂደትን በተመለከተ</u>

62.ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶች ለመንግስት ጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

63.በኦዲቱ እንደታየው ኤጀንሲው መድሃኒቶችን ወደ ጤና ተቋማት የሚያሰራጨው በመድሃኒት አያያዝ ዙሪያ ትምህርት ባልወሰዱ ሹፌሮች አማካይነት ነው፡፡

64.ለኤጀንሲው ቅርንጫፍ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በቀረበላቸው መጠይቅ፤ ባለው የሰው ኃይልና የበጀት ውሱንነት ምክንያት ሹፌሮች መድሃኒቶችን በጥንቃቄ ለጤና ተቋማት እንዲያደርሱ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

65.ሆኖም መድሃኒቶችን በሹፌሮች ኃላፊነት ረጅም ጉዞ አድርገው እንዲሰራጩ መደረጉ በጉዞ ወቅት የሚያስፈልጉ ሙያዊ ጥንቃቄዎች በአግባቡ እንዳይደረጉና ሹፌሮች መድሃኒቶቹን ይዘው ወደ ጤና ተቋማት ሲደርሱ ከባለሙያዎች ጋር በሚደረግ ርክክብ ወቅት አለመግባባቶች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ፍላጎት ጥያቄ አቀራረብን እና በፍላጎት መሰረት ማቅረብን በተመለከተ

<u>የጤና ተቋማት የመድሃኒት ፍላጎት ጥያቄ አቀራረብን በተመለከተ</u>

66.በመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት መመሪያ መሰረት መንግስታዊ የጤና ተቋማት በሙሉ የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ ሊያቀርቡ እና የመድኃኒት ትዕዛዝ የሚያቀርቡበት ጊዜ በአማካይ በየሁለት ወር መሆን አለበት፡፡

67.በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ጤና ተቋማት ከጋምቤላ ሆስፒታል በስተቀር የመድሃኒት ፍላጎታቸውን የሚያቀርቡት ለክልሉ ጤና ቢሮ ነው፡፡ የጉቴ ጤና ጣቢያና በአካባቢው ያሉ 3

ጤና ጣቢያዎች የመድሃኒት ፍላጎታቸውን ለወረዳው ጤና ፅ/ቤት ያቀርባሉ፡፡ የመድሃኒት ፍላጎት ማቅረቢያ ጊዜን በተመለከተ ጤና ተቋማት የፕሮግራም መድሃኒት ፍላጎታቸውን በየሁለት ወሩ ቢያቀርቡም ለመደበኛ መድሃኒቶች የፍላጎት ማቅረቢያ ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ የላቸውም፡፡

68. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው እንዳብራሩት በመላው ሃገሪቱ ያሉትን ጤና ተቋማት ለመድረስ ባለው የአቅም ውሱንነት እና አንዳንድ ክልሎች ለጤና ተቋማት የመድሃኒት መግዣ በጀት ወደ ወረዳ እንዲወርድ ስላላደረጉ ኤጀንሲው በየአካባቢው የሚገኙ ጤና ፅ/ቤቶችን እንደ አማራጭ እየተጠቀመ መሆኑንና ለመደበኛ መድሃኒቶች ጤና ተቋማት ሲፈልጉ መጠየቅ እንጂ ቋሚ የፍላጎት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

69. ጤና ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው አለማቅረባቸው መድሃኒቶች በፍላጎታቸው መሰረት እንዳይቀርቡላቸውና ከሌሎች ተቋማት የፍላጎት ጥያቄ ጋር መደበላለቅ እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ለጤና ተቋማት ወጥ የሆነ የመድሃኒት ፍላጎት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ ኤጀንሲው የተስተካከለ የመድሃኒት ፍላጎት ትንበያ እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የመድሃኒቶች ስርጭትን ለጤና ተቋማትና ቅርንጫፎች አስቀድሞ ማሳወቅን በተመለከተ</u>

70. በየቅርንጫፉ አገልግሎት የሚያገኙ መንግስታዊ የሕክምና ጤና ተቋማት የመድኃኒት ፍላጎት ትዕዛዝ የሚያቀርቡበትና መድኃኒት ከቅርንጫፉ የሚላክላቸዉን የጊዜ ሰሌዳ በቅድምያ ተዘጋጅቶ እንዲያዉቁት መደረግ አለበት፡፡ ከማዕከል የተመደበውና በፕሮግራም የተደለደለው መድኃኒት ለቅርንጫፎች ከመተላለፉ በፊት በቅድሚያ ቅርንጫፎች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

71. የፕሮግራም መድሃኒቶች ከኤጀንሲው ለጤና ተቋማት በአማካይ በየሁለት ወሩ ቢቀርቡም ወጥ የሆነ የማቅረቢያ ቀኑን እንዲያውቁትና ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ አይደረግም፡፡ በተጨማሪም መድሃኒቶች ከማዕከል ወደ ቅርንጫፍ የሚሰራጩበትን ቀን የማሳወቅ ሂደቱም ወጥ እንዳልሆነ ለኤጀንሲው ቅርንጫፍ ኃላፊዎች በተደረገ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የቅርንጫፍ ኃላፊዎች እንዳብራሩት የፕሮግራም መድሃኒቶችን በአማካይ በየሁለት ወሩ ለጤና ተቋማት ለማቅረብ ቢሞከርም፣ ባለው የማጓጓዣ እጥረት ምክንያት ወጥ የሆነ ቀን ተዘጋጅቶ ጤና ተቋማት ቀድመው እንዲያውቁት ለማድረግ አልተቻለም፡፡ ከማዕከል ለቅርንጫፎች የሚደረገውን የመድሃኒት ስርጭት በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ችግሩን ለመቅረፍ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

73.ጤና ተቋማት ከኤጀንሲው መድሃኒት የሚላክበትን ቀን ቀድመው እንዲያውቁት ባለመደረጉ ባለሙያዎች ተዘጋጅተውና መጋዘኖችን ለርክክብ አመቻችተው እንዳይጠብቁ እንዲሁም ቅርንጫፎች ከማዕከል መድሃኒት የሚላክበትን ቀን ወጥ በሆነ መልኩ እንዲያውቁት አለመደረጉ ቅርንጫፎች መጋዘናቸውን አዘጋጅተው እንዳይጠብቁ አድርጓል፡፡

<u>መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማት ማጓጓዝን በተመለከተ</u>

74.የማዕከል መጋዘኖችና ቅርንጫፎች አገልግሎት ለሚሰጧቸው የመንግስት ጤና ተቋማት በሚወጣው የስርጭት ፕሮግራም መሰረት እስከ ተቋማቱ በማጓጓዝ ማስረከብ አለባቸው፡፡

75.ቅርንጫፎች መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማቱ በማጓጓዝ ማስረከብ ቢኖርባቸውም፣ ለመደበኛ መድሃኒቶች እና የፀረ ኤችአይቪ ኤድስ ክትትል ለማይሰጡ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን እስከ ተቋማት የማጓጓዝ አገልግሎት አይሰጡም፡፡

76.የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለጉዳዩ እንዳብራሩት፣ ለሁሉም ተቋማት የመድሃኒት ማጓጓዝ አገልግሎቱን ወደፊት ለመጀመር እንደ ዕቅድ ይዘው እየሰሩ መሆኑንና ዕቅዱንም ለማሳካት የሙከራ ትግበራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

77.ኤጀንሲው መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማቱ ድረስ በማጓጓዝ አለማስረከቡ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን ለመውሰድ ተጨማሪ የማጓጓዣ ወጪ እንዲያወጡ አድርጓል፡፡

<u>መድሃኒቶችን በጤና ተቋማት ፍላጎት መሰረት ማቅረብን በተመለከተ</u>

78.ለጤና ተቋማት የሚደረገው የመድኃኒት ክፍፍል የጤና ተቋሙ በሚልከው የመድኃኒት ፍላጎት መሰረት መሆን አለበት፡፡

79.በናሙና ከታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በነቀምት ቅርንጫፍ ስር የጉቴ ጤና ጣቢያ፣ የኡኬ ጤና ጣቢያ እና የነቀምቴ ሪፈራል ሆስፒታል እንዲሁም በጅማ ቅርንጫፍ ስር የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የአጋሮ ጤና ጣቢያ፣ የሰርቦ ጤና ጣቢያ፣ የቦንጋ ጤና ጣቢያ፣ የጋምቤላ ጤና ጣቢያ እና የጋምቤላ ሆስፒታል የሚላክላቸው መድሃኒት ፍላጎታቸውን መሰረት ከማድረግ ይልቅ መድሃኒቶች በግዴታ እንደሚላኩላቸው ታይቷል፡፡ በተመሳሳይ በደሴና ባህርዳር ቅርንጫፍ ግልጋሎት የሚያገኙ ጤና ተቋማትም የችግሩ ተጠቂ እንደሆኑ ታይቷል፡፡

80.ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ኃላፊዎች እንዳብራሩት አንዳንዴ ሂደቱ ተፈፃሚ የሚሆነው በፕሮግራም መድሃኒቶች አቅርቦት ላይ መሆኑንና ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸሻለና መድሃኒቶችን በጤና ተቋማት ፍላጎት መሰረት ለማሰራጨት እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

81. መድሃኒቶች የጤና ተቋማትን ፍላጎት መሰረት ባላደረገ መልኩ መሰራጨታቸው፣ ጥቅም ላይ ሳይውሉ እንዲከማቹና ለብልሽት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የተቃረቡ መድሃኒቶች ስርጭትን በተመለከተ</u>

82. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድሃኒቶች ለጤና ተቋማት መሰራጨት የለባቸውም፡፡

83. በናሙና ከታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በነቀምት ቅርንጫፍ ስር የጉቴ ጤና ጣቢያ፣ የኡኬ ጤና ጣቢያ እና የነቀምቴ ሪፈራል ሆስፒታል እንዲሁም በጅማ ቅርንጫፍ ስር የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የአጋሮ ጤና ጣቢያ፣ የሰርቦ ጤና ጣቢያ፣ የቦንጋ ጤና ጣቢያ፣ የጋምቤላ ጤና ጣቢያ እና የጋምቤላ ሆስፒታል የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድሃኒቶች እንደሚሰራጩላቸው ታይቷል፡፡ ችግሩ በተመሳሳይ በደሴና ባህርዳር ቅርንጫፎች ስር ባሉ ጤና ተቋማትም ተስተውሏል፡፡

84. የኤጀንሲው የቅርንጫፍ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው እንዳብራሩት፣ ችግሩ የሚከሰተው መድሃኒቶቹ ከማዕከል ለቅርንጫፎች ሲሰራጩ አጭር የመጠቀሚያ ጊዜ ይዘው ስለሚመጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

85. የኤጀንሲው የማዕከል ኃላፊዎች በበኩላቸው ስለችግሩ ተጠይቀው እንዳብራሩት፣ ባለው የመድሃኒት ማከማቻ ቦታ ጥበትና አለመመቸት ምክንያት በቅድሚያ መሰራጨት የነበረባቸው አጭር መጠቀሚያ ጊዜ ያላቸው መድሃኒቶች ተቀምጠው ረጅም መጠቀሚያ ጊዜ ያላቸው መድሃኒቶች እንዲሰራጩ የሚደረግበት ወቅት መኖሩ ለችግሩ መከሰት ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም በእርዳታ የተገኙ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ግብዓቶች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አኳያ እየታየ ስርጭት እንደሚካሄድ ገልፀዋል፡፡

86. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድሀኒቶች ለጤና ተቋማት መሰራጨታቸው በጤና ተቋማት ጥቅም ሳይሰጡ እንዲበላሹና የማከማቻ ቦታ ጥበት እንዲፈጥሩ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

<u>የመድሃኒቶች ማጓጓዣ ስርዓትና የመድን ሽፋንን በተመለከተ</u>

87. ኤጀንሲው መንግስታዊ ጤና ተቋማት ላይ በሚያደርገው ጉብኝትና ምልከታ መሰረት የተጠናከረ የማጓጓዣ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

88. በኦዲቱ እንደታየው ለኤጀንሲው ቅርንጫፎች የተመደቡት የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ቅርንጫፎቹ መድሃኒት ከሚያሰራጩላቸው ጤና ተቃማት ብዛት ጋር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ ነው፡፡ ለቅርንጫፎች የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እና አገልግሎት የሚሰጧቸው ጤና ተቋማት ብዛት በቀጣዩ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	ቅርንጫፍ	የተመደበለት የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ብዛት	አገልግሎት የሚሰጣቸው ጤና ተቋማት ብዛት	አንድ ተሽከርካሪ በአማካይ የሚያገለግለው ጤና ተቋም ብዛት
1.	ጅማ	5	340	68
2.	ነቀምቴ	6	541	90
3.	ባህርዳር	7	150	21
4.	ደሴ	4	270	67
5.	አዲስአበባ	5	398	80

ሰንጠረዥ 2- የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪና ጤና ተቋማት ብዛት በቅርንጫፎች

89. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ችግሩ ካለው የግብዓት ውሱንነት የመነጨ እንደሆነና ችግሩን ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎች (ለምሳሌ- የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት) እየተወሰዱ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

90. ለመድሃኒት ስርጭት በቂና ካሉት ጤና ተቋማት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ለቅርንጫፎች አለመመደቡ የተቆራረጠና ወጥነት የጎደለው የመድሃኒት ስርጭት ስርዓት እንዲኖር አድርጓል፡፡

91. ከማዕከል መጋዘኖች ወደ ቅርንጫፎች ፤ ከቅርንጫፎች ወደ ማዕከል እና በቅርንጫፎች መካከል ለሚደረጊዉ የመድኃኒቶች ዝዉዉር በጉዞ ወቅት ለሚከሰት አደጋ እንደ አስፈላጊነቱ እና አመቺነቱ የመድን ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

92. ከቅርንጫፎች ወደ ማዕከል፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፎ እና ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋማት ለሚደረግ የመድሃኒት ዝውውር የመድን ሽፋን አይገባም፡፡

93. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች እንደገለፁት ከማዕከል ወደ ቅርንጫፎች ለሚላኩ መድሃኒቶች የመድን ሽፋን እንደሚገባና ለሌሎችም የመድሃኒት ዝውውሮች እንደአስፈላጊነቱ የመድን ሽፋን መገባት እንደነበረበት ደግፈዋል፡፡

94. ለሚደረጉ የመድሃኒት ዝውውሮች እንደአስፈላጊነቱ የመድን ሽፋን አለመገባቱ በመድሃኒቶቹ ላይ በጉዞ ወቅት ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች የማካካሻ ማስተማመኛ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

የመድኃኒት አያያዝ፣ አስተዛዘዝ እና አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠርን በተመለከተ

95.የመድኃኒት አስተዛዘዝ፣ ዕደላና አጠቃቀም እንዲሁም በመድኃኒት ጎጂ ባህሪያት ዙሪያ የባለሙያ ክህሎት የሚጎለብትበት ተከታታይ ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

96. በኦዲቱ እንደታየው በኤጀንሲው በመደበኛነት የሚሰጠው የ IPLS (Integerated Pharmaceuticals Logistics Supply) ስልጠና ትኩረት የሚያደርገው የመድሃኒት አያያዝና አቀማመጥ ላይ ሲሆን፣ በመድሃኒት አስተዛዝ፣ ወጪ አደራረግ እና ግንዛቤ መፍጠር ላይ ከመድኒት መጋዘን ውጪ የሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎችን ክህሎት በማዳበር ዙሪያ ክፍተት አለበት፡፡

97.የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ እስካሁን ኤጀንሲው ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ የነበረው በመድሃኒት ክምችት አስተዳደር ዙሪያ እንደነበረና አቅም የማጎልበት ሥራው ተጠናክሮ ከመጋዘን ውጭ ለሚሰሩትም ባለሙያዎች በወጪ አደራረግ ዙሪያ ክህሎታቸው ቢዳብር መልካም መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98.በመድሃኒት ወጪ አደራረግ ዙሪያ ከመድኃኒት መጋዘን ውጪ ለሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎች ግንዛቤ አለመፈጠሩ ባለሙያዎቹ ከመድሃኒት መጋዘን ኃላፊዎች ጋር በመድሃኒቶች ወጪ አደራረግ ላይ ለተደጋጋሚ ክርክርና አለመግባባት ሊዳርግ ይችላል፡፡

99.የኤጀንሲውን ራዕይ ለማሳካት በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይነት ያለው ትምህርት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

100. በኦዲቱ ተመርጠው በታዩት የጅማ፣ ነቀምቴ፣ ባህርዳር፣ ደሴ እና አዲስአበባ ባሉት የኤጀንሲው ቅርንጫፎች በመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰራ ሥራ ተጠይቆ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

101. ስለጉዳዩ የቅርንጫፍ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ቅርንጫፎች በተናጠል ወጪና ግዥዎችን መፈፀም ስለማይችሉ በሬዲዮና መሰል መገናኛ ብዙሃን ስለመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ትምህርት መስጠት አለመጀመራቸውን አስረድተዋል፡፡ የማዕከል ኃላፊዎች በበኩላቸው ግንዛቤ የመፍጠር ስራው በማዕከል ደረጃ በራዲዮ (FM 98.1) እና በተለያዩ ህትመቶች እየተሰራ እንደሆነና በስፋት በቅርንጫፎች ደረጃ በተደራሽ ቋንቋዎች ለመስራት እቅድ እንዳለ አስረድተዋል፡፡

102. ሆኖም ስለ መድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ለህብረተሰቡ ትምህርቶች በተለያዩ ቋንቋዎችና ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መልኩ አለመሰጠታቸው ኤጀንሲው እንደ ራዕይ አስቀምጦ እየሰራለት የሚገኘውን አግባብ ያለው የመድሃኒት አጠቃቀም መፍጠር የሚል ፅንሰ-ሃሳብ ሙሉ በሙሉ እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በመድሃኒት ክምችትና ስርጭት ዙሪያ ኤጀንሲው ያለውን የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት እና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

103. የመድኃኒት ፍላጎት ለመተንበይ፣ ብክነትና እጥረትን ለመከላከል የሚያስችል የተጠናከረ የመረጃ ኔትዎርክ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

104. ኤጀንሲው አጠቃላይ የመደሃኒቶችን ክምችትና ስርጭት ለመከታተል እንዲያስችለው በቅርንጫፎችና ጤና ተቋማት የተቀናጀ የመድሃኒትና መገልገያዎች ክምችትና አቅርቦት ስርዓትን (Integrated Pharmaceuticals Logistics and Supply System- IPLS) ዘርግቶ ወደ ሥራ ቢገባም፣ ስርዓቱ በመረጃ ኔትዎርክ ተያይዞ ቅርንጫፎች የጤና ተቋማትን ክምችት እንዲቆጣጠሩ የሚያስችል እንዳልሆነ በኦዲቱ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም በናሙና ከታዩ ጤና ተቋማት መካከል ጋምቤላ፣ ኡኬ፣ ጉቴና አጋሮ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በጳውሎስና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች የ IPLS ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

105. የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአንዳንድ ጤና ተቋማት ያለው የሰው ሃይል በተደጋጋሚ መልቀቅ ስርዓቱ በአግባቡ እንዳይከናወን ምክንያት መሆኑንና በሁሉም ተቋማት በመረጃ ኔትዎርክ የተሳሰረ የመድሃኒት ክምችት ስርዓት ለመፍጠር ዕቅድ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

106. በመረጃ ኔትዎርክ የተሳሰረ የመድሃኒት ክምችት ስርዓት አለመፈጠሩ ኤጀንሲው የጤና ተቋማትን የመድሃኒት ክምችት ሁኔታ በቀጥታ እየተከታተለ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዳይወስድ ምክንያት ሆኗል፡፡

107. ቅርንጫፎች ለኤጀንሲው በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት የሚያቀርቡበት እና ግብረ መልስ የሚሰጡበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

108. ቅርንጫፎች ለኤጀንሲው ሪፖርት ቢያቀርቡም ለሪፖርቶቹ ከማዕከል የሚሰጠው ግብረ-መልስ የተጠናከረ እንዳልሆነ በኦዲቱ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት አጠቃላይ የመድሃኒት አጠቃቀም ሪፖርት ለኤጀንሲው አያቀርቡም፡፡

109. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች እንዳስረዱት ለሪፖርቶች የሚሰጠው ግብረ-መልስ በሚደረጉ ግምገማዎች ወቅት በቃል እንደሆነና የተጠናከረ እንዳልሆነ፤ ጤና ተቋማትም ለፕሮግራም

መድሃኒቶች በየሁለት ወሩ ከሚልኩት ሪፖርት ውጪ አጠቃላይ ሪፖርት እንደማያቀርቡ ገልፀዋል፡፡

110. ከቅርንጫፎች ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ተገቢው ግብረ-መልስ በማዕከል አለመሰጠቱ በቅርንጫፎች እንደ ችግር የሚጠቀሱ ጉዳዮች በቶሎ ሳይፈቱ በሪፖርቶች ውስጥ በተደጋጋሚ እንደ ችግርነት እየተጠቀሱ እንዲቀጥሉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት አጠቃላይ የመድሃኒት ፍጆታና አጠቃቀም ሪፖርታቸውን ለኤጀንሲው ሪፖርት አለማድረጋቸው መረጃውን ኤጀንሲው ለቀጣይ የመድሃኒት ፍላጎት ትንበያ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያዎች

ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችትና ስርጭትን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው ቅርንጫፎችና መንግስታዊ ሕክምና መስጫ ተቋማት የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡፡

111. የመድሃኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች አቅርቦት ላይ መቆራረጥ መኖሩ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን ከግል አቅራቢዎች እንዲገዙና በመድሃኒት ግዥ ሥራ እንዲጠመዱ ምክንያት ሲሆን፤ በመንግስት ጤና ተቋማት የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችትን በተመለከተ በኤጀንሲው የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር የተጠናከረና ወጥ የጊዜ ሰሌዳ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ኤጀንሲው በተቋማቱ ያሉትን ችግሮች ለይቶ የማሻሻያ ሃሳቦች እንዳይሰጥና በጤና ተቋማት ተገቢ ያልሆነ የመድሃኒት ክምችት እንዲኖር አድርጓል፡፡
112. በሁሉም ክልሎች የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ባለመኖራቸውና ያሉትም መጋዘኖች በዘመናዊ መልክ ባለመደራጀታቸው እንደ ደሴ ባሉት የኤጀንሲው ቅርንጫፎች መድሃኒቶች ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከመጋዘን ውጪ እንዲከማቹና ችግሩ ሳይፈታ እንዲቀጥል አድርጎታል፡፡
113. ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በመንግስት ጤና ተቋማት አለመሟላታቸው ተገቢ የሆነ የመድሃኒት አከመቻቸት ስርዓትን ለመፍጠር እንቅፋት ፈጥሯል፡፡
114. ተለይተው በጥንቃቄ መቀመጥ ያለባቸው መድሃኒቶች ከሌሎች መድሃኒቶች ጋር ተቀላቅለው ያለጥንቃቄ መከማቸታቸው ተገቢና ጥንቃቄ የተሞላበት የመድሃኒት ክምችት ስርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡
115. የመድሃኒት ክምችት መጠን አመላካቾች በጤና ተቋማት ስራ ላይ አለማዋላቸው ተቋማቱ ያላቸውን የክምችት መጠን አውቀው፣ መድሃኒቶች ከማለቃቸው በፊት አስቀድመው ለማዘዝ እንዳይችሉ አድርጓል፡፡
116. ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ ክምችት ያላቸው ጤና ተቋማት ለኤጀንሲው ሪፖርት አለማድረጋቸው መድሃኒቶች ጥቅም ሳይሰጡ የአገልግሎት ማብቂያቸው እንዲያልፍ እና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ሳይሰጡ በክምችት እንዲቆዩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት በክምችት የሚገኙ መድሃኒቶችን ይዘት ሪፖርት አለማድረጋቸው ኤጀንሲው በተቋማቱ ያለውን የክምችት መጠን እንዳይከታተልና መረጃውን ለቀጣይ የመድሃኒት ስርጭት ዕቅድ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

117. የተጠናቀረ የቅርንጫፎች የቆጠራ ሪፖርት በጊዜው አለመቅረቡ፣ የጤና ተቋማትን የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ቆጠራ ውጤት አለማወቁ እና በሥራ ሂደት የተሰበሩና የተበላሹ መድኃኒቶች ቋሚ በሆነ የመድሃኒት የጊዜ ሰሌዳ ሪፖርት አለመደረጋቸው ኤጀንሲው እንደ አጠቃላይ በአዲስ በጀት ዓመት በእጁ ያሉትን ግብዓቶች ዝርዝር እንዳያውቅና መረጃውን ለክትትል፣ ቁጥጥር እና ለቀጣይ ዓመት ዕቅድ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

118. አግባብ ያለው የመድሃኒት አወገገድ ስርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ የሚወገዱ መድሃኒቶች በአካባቢውና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ጉዳት እንይታወቅና እንዳይቀንስ ሆኗል፡፡

119. የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አለመወገዳቸውና የአገልግሎት ማብቂያቸው ሳያልፍ ግልጋሎታቸው በሌላ የተተኩ መድሃኒቶችን በተመለከተ አቅጣጫ አለመቀመጡ ከፍተኛ የሆነ የመድሃኒት ክምችት እንዲፈጠርና ለማስወገድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

120. የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመወገዳቸው እንደ ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል ባሉ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ የተበላሹ መድሃኒቶች ክምችት እንዲፈጠርና ለማስወገድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በቅርንጫፎችና በጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ጥቅም የማይሰጡ ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ለጉዳዩ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ መሳሪያዎቹ ወደ ሌላ ተቋም ተዘዋውረው ጥቅም ሊሰጡ የሚቻልበት እድል እንዳይፈጠር እንዲሁም ጥቅም የማይሰጡት አግባብ ባለው ሁኔታ እንዳይወገዱና የማከማቻ ቦታ ጥበት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

121. ለመድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ብልሽት እና ጥቅም ላይ አለመዋል እንደ መንስዔ ሊጠቀሱ የሚችሉ ጉዳዮችን የሚያሳይ ጥናት በቅርንጫፎች አለመደረጉ ኤጀንሲው ለመድሃኒት ብልሽት ዋና ምክንያቶችን ለይቶ ችግሩን ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ እንዳይወስድ አድርጓል፡፡

122. መድሃኒቶችን በሹፌሮች ኃላፊነት ረጅም ጉዞ አድርገው እንዲሰራጩ መደረጉ በጉዞ ወቅት የሚያስፈልጉ ሙያዊ ጥንቃቄዎች በአግባቡ እንዳይደረጉና ሹፌሮች መድሃኒቶቹን ይዘው ወደ ጤና ተቋማት ሲደርሱ ከባለሙያዎች ጋር በሚደረግ ርክክብ ወቅት አለመግባባቶች እንዲከሰቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

123. በግዥ ለሚወሰዱ መደበኛ መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋማቱ ስለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ባለመኖሩ የመድሃኒት ማጭበርበር ችግሮች ተከስተዋል፡፡

124. ጤና ተቋማት የመድሃኒት አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው አለማቅረባቸው መድሃኒቶች በፍላጎታቸው መሰረት እንዳይቀርቡላቸውና ከሌሎች ተቋማት የፍላጎት ጥያቄ ጋር

መደበላለቅ እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ለጤና ተቋማት ወጥ የሆነ የመድሃኒት ፍላጎት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ ኤጀንሲው የተስተካከለ የመድሃኒት ፍላጎት ትንበያ እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡

125. ጤና ተቋማት ከኤጀንሲው መድሃኒት የሚላክበትን ቀን ቀድመው እንዲያውቁት ባለመደረጉ ባለሙያዎች ተዘጋጅተውና መጋዘኖችን ለርክክብ አመቻችተው እንዳይጠብቁ እንዲሁም ቅርንጫፎች ከማዕከል የሚደለደልላቸውን መድሃኒት ብዛት እና የሚላክበትን ቀን ወጥ በሆነ መልኩ እንዲያውቁት አለመደረጉ ቅርንጫፎች ለጤና ተቋማት የሚያሰራጩትን መድሃኒት ብዛት እንዳያውቁትና መጋዘናቸውን አዘጋጅተው እንዳይጠብቁ አድርጓል፡፡

126. ኤጀንሲው መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማቱ ድረስ በማጓጓዝ አለማስረከቡ ጤና ተቋማት ለተጨማሪ የማጓጓዣ ወጪ እንዲዳረጉ አድርጓል፡፡

127. የፕሮግራም መድሃኒቶች የጤና ተቋማትን ፍላጎት መሰረት ባላደረገ መልኩ መሰራጨታቸው ጥቅም ላይ ሳይውሉ እንዲከማቹና ለብልሽት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆኗል፡፡

128. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድሀኒቶች ለጤና ተቋማት መሰራጨቱ በጤና ተቋማት ጥቅም ሳይሰጡ እንዲበላሹና የማከማቻ ቦታ ጥበት እንዲፈጥሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

129. ለመድሃኒት ስርጭት በቂና ካሉት ጤና ተቋማት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ለቅርንጫፎች አለመመደቡ የተቆራረጠና ወጥነት የጎደለው የመድሃኒት ስርጭት ስርዓት እንዲኖር አድርጓል፡፡

130. ለሚደረጉ የመድሃኒት ዝውውሮች እንደአስፈላጊነቱ የመድን ሽፋን አለመገባቱ በመድሃኒቶቹ ላይ በጉዞ ወቅት ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች የማካካሻ ማስተማመኛ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

131. በመድሃኒት ወጪ አደራረግ ዙሪያ ከመድኒት መጋዘን ውጪ ለሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎች ግንዛቤ አለመፈጠሩ በመድሃኒቶች ወጪ ማድረጊያ ቅፅ አሞላል ላይ በሚፈጠር ክፍተት ባለሙያዎቹ ከመድሃኒት መጋዘን ኃላፊዎች ጋር በተደጋጋሚ ክርክርና አለመግባባት ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

132. ስለ መድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ለህብረተሰቡ ትምህርቶች በተለያዩ ቋንቋዎችና ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መልኩ አለመሰጠታቸው ኤጀንሲው እንደ ራዕይ አስቀምጦ እየሰራለት የሚገኘውን አግባብ ያለው የመድሃኒት አጠቃቀም መፍጠር የሚል ፅንሰ-ሃሳብ ሙሉ በሙሉ እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

133. በመረጃ ኔትዎርክ የተሳሰረ የመድሃኒት ክምችት ስርዓት አለመዘርጋቱ ኤጀንሲው የጤና ተቋማትን የመድሃኒት ክምችት ሁኔታ በቀጥታ እየተከታተለ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዳይወስድ ምክንያት ሆኗል፡፡

134. ከቅርንጫፎች ለሚቀርቡ ሪፖርቶች የተጠናከረ ግብረ-መልስ በማዕከል አለመሰጠቱ በቅርንጫፎች እንደ ችግር የሚጠቀሱ ጉዳዮች በቶሎ ሳይፈቱ በሪፖርቶች ውስጥ በተደጋጋሚ እንደ ችግርነት እየተጠቀሱ እንዲቀጥሉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ጤና ተቋማት አጠቃላይ የመድሃኒት ፍጆታና አጠቃቀም ሪፖርታቸውን ለኤጀንሲው ሪፖርት አለማድረጋቸው መረጃውን ኤጀንሲው ለቀጣይ የመድሃኒት ፍላጎት ትንበያ እንደ ግብዓት እንዳይጠቀመው አድርጓል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

ከላይ በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶችና መደምደሚያዎች መሰረት የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡-

135. ኤጀንሲው የመድሃኒቶች፣ ኬሚካሎችና ላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች አቅርቦቱን ሊያሻሽል ይገባል፡፡

136. የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ክምችትን በተመለከተ በኤጀንሲው ቅርንጫፎች የሚደረገው የጤና ተቋማት ምልከታ፣ ክትትል እና ቁጥጥር ወጥ በሆነና ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ሊከናወንና በምልከታውም መሰረት ተገቢው የማሻሻያ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

137. በተለያዩ ክልሎች እየተከናወኑ ያሉት የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ግንባታ በቶሎ ተጠናቆ መጋዘኖቹ ወደ ሥራ መግባት አለባቸው፡፡

138. ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በመንግስት ጤና ተቋማትም ሆነ በኤጀንሲው ቅርንጫፍ መጋዘኖች ሊሟሉና ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

139. ተለይተው በጥንቃቄ መቀመጥ ላለባቸው መድሃኒቶች ተገቢው ጥንቃቄና ጥበቃ ሊደረግ ይገባል፡፡

140. የመድሃኒት ክምችት መጠን አመላካቾች በሁሉም ቅርንጫፎችና ጤና ተቋማት ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

141. ጤና ተቋማት በክምችት የሚገኙ መድሃኒቶችን ይዘት እንዲሁም በእጃቸው ያለውን ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያ ክምችት ለኤጀንሲው ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

142. የቅርንጫፎች የቆጠራ ሪፖርት ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለማዕከል ሊላክና የመንግስታዊ ጤና ተቋማት የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ቆጠራ ሪፖርት ለኤጀንሲው ሊቀርብ ይገባል፡፡

143. በጤና ተቋማትና በቅርንጫፎች ስር በሥራ ሂደት የተሰበሩና የተበላሹ መድኃኒቶች ቋሚና ወጥ በሆነ የጊዜ ሰሌዳ ሪፖርት ሊደረጉ ይገባል፡፡

144. አግባብ ያለው በአካባቢና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት የማያደርስ የመድሃኒት አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

145. የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በየ 3 ወሩ ሊወገዱ እና የአገልግሎት ማብቂያቸው ሳያልፍ ግልጋሎታቸው በሌላ ዓይነቶች ለተተኩ መድሃኒቶች ኤጀንሲው የመፍትሄ አቅጣጫ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

146. ለመድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ብልሽት እና ጥቅም ላይ አለመዋል እንደ መንስዔ ሊጠቀሱ የሚችሉ ጉዳዮችን የሚያሳይ ጥናት ተሰርቶ ችግሩን ለመቀነስ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

147. በጤና ተቋማትና በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጥቅም ሳይሰጡ ተከማችተው የሚገኙ የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር ተለይቶ ጥቅም የሚሰጡበት ሁኔታ ሊመቻችና ከተበላሹም በኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ሊወገዱ ይገባል፡፡

148. የመድሃኒቶች ስርጭት ሙያዊ ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ኃላፊነት ሊደረግ፤ በሹፌሮች ኃላፊነትም ይፈፀም ከተባለ ተገቢው ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

149. በማንኛውም መልኩ ከኤጀንሲው ወደ ጤና ተቋማት ለሚወሰዱ መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋማቱ ስለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡

150. ጤና ተቋማት ለመድሃኒት ፍላጎት ማቅረቢያ ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ ሊኖራቸውና ጥያቄያቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ የሚያቀርቡበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

151. ጤና ተቋማት እና ቅርንጫፎች የሚደለደልላቸውን መድሃኒት ብዛት እና የሚላክበትን ቀን ወጥ በሆነ መልኩ እንዲያውቁት የሚደረግበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

152. ኤጀንሲው መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማቱ ድረስ በማጓጓዝ ማስረከብ አለበት፡፡

153. ኤጀንሲው መድሃኒቶችን በግዴታ ሳይሆን በጤና ተቋማቱ ፍላጎት መሰረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

154. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድሀኒቶች ለጤና ተቋማት መሰራጨት የለባቸውም፡፡

155. ለመድሃኒት ስርጭት በቂና ካሉት ጤና ተቋማት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ለቅርንጫፎች ሊመደቡ ይገባል፡፡

156. በማንኛውም ወቅት ለሚደረጉ የመድሃኒት ዝውውሮች እንደአስፈላጊነቱ የመድን ሽፋን መገባት አለበት፡፡

157. በመድሃኒት ወጪ አደራረግ እና አስተዛዘዝ ዙሪያ ከመድኒት መጋዘን ውጪ ለሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎች የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠናዎች የሚሰጡበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

158. ስለ መድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ወጥነትና ተደራሽነት ባለው መልኩ ለህብረተሰቡ ትምህርትና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

159. በመረጃ ኔትዎርክ የተሳሰረ የመድሃኒት ክምችት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

160. ከቅርንጫፎች ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ማዕከሉ ተገቢውን ግብረ-መልስ መስጠት አለበት፡፡

161. ጤና ተቋማት አጠቃላይ የመድሃኒት ፍጆታና አጠቃቀም ሪፖርታቸውን ለኤጀንሲው ሪፖርት የሚያደርጉበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

162. በአጠቃላይ በሀገሪቱ ያለው የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት ስርዓት አስፈላጊ መድሃኒቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑና ለዜጎች ጤንነት መሻሻል አወንታዊ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ብሄራዊ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና በዘርፉ የወጡ አለም አቀፍ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ አፈፃፀሙን ለመከታተል፣ የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ የኤጀንሲው፣ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላትን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ኤጀንሲውን ሙሉ ለሙሉ የማይመለከቱ ቢኖሩ፣ ኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የኤጀንሲውና በናሙና የተመረጡ የቅርንጫፍና ጤና ተቋማት ኃላፊዎችና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን በማቅረብ እና ለኦዲቱ ለቀረቡ ቃለ መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ላደረጉት ቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1- የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር





አባሪ 2- የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ጭብጥ /Issues/	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)
	የመድሃኒት እና የሕ/መገልገያዎች ርክክብን በተመለከተ፤
ደረጃቸውን የጠበቁ የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ማከማቻዎች መስፋፋታቸውንና ዘመናዊ የክምችትና የአወጋገድ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ	1. ከዉጭ ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ ማንኛውም መድሀኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ሊያሟሉት የሚገባቸው ዝርዝር መስፈርት ሊዘጋጅና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	2. ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ወደ ማዕከል የመጣ ማንኛውም መድኃኒት በግዥ ትዕዛዝ በተገለፁ ሁኔታዎችና መስፈርቶች የፕሮግራም መድኃኒት ከሆነ ደግሞ በፕሮግራሙ ትዕዛዝ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡
	3. ማንኛዉም በእርዳታ የሚሰጥ መድሀኒት አለም አቀፍ የጥራት ደረጃና ሀገሪቱ የተቀበለችዉን ደረጃ የሚያሟላና በእርዳታ ሰጭው አገር ዉስጥ ጥቅም ላይ የሚዉል መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	4. በማንኛውም መንገድ በመረከቢያ ደረሰኝ ገቢ የተደረጉ መድኃኒቶች በኮምፒዩተር የመረጃ ስርዓት ውስጥ በፅንሰ-ስም፣ በትክክለኛ ይዘት(unit) እና በአምራች ኩባንያ ስም መግባታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡
	የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ርክክብ፣ ክምችት፣ ሪፖርት አቀራረብ እና አወጋገድ ተገቢ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን እና ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፤
	5. የመድኃኒትና የሕ/መገልገያ መጋዘኖች የቦታ አከፋፈልና የክምችት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡
	6. ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና እና ያልተቋረጠ አቅርቦት የሚኖርበት ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	7. የመድኃኒት ብክነት እና እጥረት እንዳይደርስ ለመከላከል የተጠናከረ የመድኃኒት

	ክምችትና ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	8. ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ክምችት ያላቸው ቅርንጫፎችና የጤና ተቋማት ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	9. በጤና ተቋማት ውስጥ የሚታየውን የክምችት መጠን በመከታተል ከፍተኛ ክምችት ከሚታይበት ተቋም እጥረት ወደሚታይበት የሚዘዋወርበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	10. የክምችት እጥረት ወይም ከፍተኛ ክምችት የሚታይባቸው ቅርንጫፎችና የጤና ተቋማት ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	11. በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አግባብ ባለው መንገድ የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
ደረጃቸውን(Standard) የጠበቁ መጋዘኖች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች መገንባትን በተመለከተ፤	
	12. ለመድኃኒት አያያዝ አመቺ የሆኑና ለየአካባቢው የአየር ጠባይ የሚስማሙና የተደራጁ ዘመናዊ መጋዘኖች በሁሉም ክልሎች ሊቋቋም ይገባል፡፡
	13. የመረከቢያ፣ የማከማቻና የማሰረከቢያ መጋዘኖች የተለያዩ መሆን አለባቸዉ፡፡
	14. የማከማቻ መጋዘን መድኃኒቶችን እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው ለመያዝ የሚያስችል በቂ ቦታና ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎ መደራጀት አለበት፡፡
	15. የመረከቢያ፣ የማከማቻና የማስረከቢያ መጋዘኖች ንፅህናቸው የተጠበቀ፣ በቂ የመረከቢያ፣ የማከማቻና የማስረከቢያ ስፍራ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	16. ለመረከቢያ፣ ለማከማቻና ለማስረከቢያ መጋዘኖች አገልግሎት የሚውሉ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች(የሙቀት መለኪያዎች፣ ፎርክሊፍት፣ ጋሪ፣ ፓሌት፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶች ወዘተ.) መሟላት አለባቸው፡፡
መድሃኒቶችንና የሕ/መገልገያዎችን በአግባቡ ማከማቸትን በተመለከተ፤	
	17. መድሃኒቶች በአይነት፣ በባች ቁጥር፣ በመጠቀሚያ ጊዜ ማብቂያ (First expired first out(FEFO)) ተለይተው ገቢ መደረግና መቀመጥ አለባቸው፡፡
	18. ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ቁልፍ ባለው የብረት ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል መቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት ባለሙያ እጅ መሆን አለበት፡፡
	19. በተገላባጭ(revolving) የመድኃኒት ፈንድ የቀረቡና በፕሮግራም የቀረቡ መድኃኒቶች ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን መቀመጥ የለባቸውም፡፡
	20. በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በመንግስታዊ የሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት የሚኖረዉ የክምችት መጠን ከሚፈለገዉ በታች ወይም በላይ እንዳይሆን ወይም በአጠቃላይ ከክምችት ጠፍቶ ችግር እንዳይፈጠር የክምችት መጠን አመላካቾች (Average monthly consumption, Minimum stock level, safety stock Level) በየደረጃዉ (በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንድሁም በጤና ተቋሞች) በሥራ ላይ ማዋል አለባቸዉ፡፡
የመድሃኒቶችን ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ፤	
	21. በማከማቻ መጋዘን የሚገኘዉን የክምችት ይዘት ዕለት ከዕለት በሚኖረዉ የመረጃ ስርዓት በመከታተል ለሚመለከተዉ አስፈላጊዉ መረጃ (ከፍተኛ ክምችት የሚታይባቸዉ፣ አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸዉ የመጠቀሚያ ዘመናቸዉ ለማብቃት የተቃረቡ ወዘተ) መተላለፍ አለበት፡፡
	22. ማንኛዉም በኤጀንሲዉ የሚገኝ የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ክምችት ቆጠራ በበጀት ዘመኑ ማብቂያ መደረግ እና የቆጠራው ዉጤት ከሐምሌ 30 በፊት ተጠቃሎ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡
	23. በሥራ ሂደት የተሰበሩና የተበላሹ መድኃኒቶች በየ3 ወር እና ዓመታዊ ቆጠራ ከመከናወኑ በፊት ዝርዝራቸዉን ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት በማድረግ ዉሳኔ ተሰጥቶበት በኮሚቴ እንዲወገዱ መደረግ አለበት፡፡

	የተበላሹ መድኃኒቶችን በአግባቡ ማስወገድን በተመለከተ፤
	24. የሚወገዱት መድኃኒቶችና የሕ/መገልገያዎች በዓይነት፣ በመጠን እንዲሁም በዋጋ መለየት አለባቸው፡፡
	25. የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕ/መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ በማወቅ ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡
	26. የሚወገዱ መድኃኒቶችና የሕ/መገልገያዎች ከሚመለከተው አካል የማስወገጃ ፈቃድ እና ቦታ ማግኘት አለባቸው፡፡
	27. በማዕከልና ቅርንጫፍ መጋዘኖች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በየሩብ አመት መጨረሻ የተቆጣጣሪ ባለስልጣን ተወካዮች ባሉበት እንዲወገዱ ተደርጎ የማስወገጃ ሰርተፊኬት (Disposal certificate) በወቅቱ እንዲቀርብ ክትትል መደረግ አለበት፡፡
	28. ለተጠቃሚው ቀርበው ለ5 ዓመት እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው(በሚፈለገው መልኩ ለተጠቃሚው አገልግሎት የማይሰጡ) የሕ/መሳሪያዎች ዝርዝር ለሚመለከተው አካል እየቀረቡ እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡
ደረጃቸውን የጠበቁ የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች የስርጭት አውታሮች መስፋፋታቸውንና በወቅቱ ለጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ	**የስርጭት ስርዓት ማዘጋጀትን በተመለከተ፤**
	29. ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶች ለመንግስት ጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	30. በበቂ መጠን ሊቀርቡ ያልቻሉ የተመረጡ መድኃኒቶችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መንግስታዊ ላልሆነና ለግል የጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	31. የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የማሰራጨት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊነቱ ሊገመገም ይገባል፡፡
	32. ከማዕከል መጋዘኖች ለቅርንጫፎች መድኃኒት የሚላክበት የጊዜ ሰሌዳ (መርሃ ግብር) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	33. ለጤና ተቋማት ወጪ የሚደረገው መድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ወደ ተቋማቱ ለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	የመድኃኒትና የሕ/መገልገያዎች ፍላጎት ጥያቄን በተመለከተ፤
	34. መንግስታዊ የጤና ተቋማት በሙሉ የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
	35. መንግስታዊ የሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት ለኤጀንሲዉ የመድኃኒት ማከፋፈያዎች የመድኃኒት ትዕዛዝ የሚያቀርቡበት ጊዜ በአማካይ በየሁለት ወር መሆን አለበት፡፡
	36. በየቅርንጫፉ አገልግሎት የሚያገኙ መንግስታዊ የሕክምና ጤና ተቋማት የመድኃኒት ፍላጎት ትዕዛዝ የሚያቀርቡበትና መድኃኒት ከቅርንጫፉ የሚላክላቸዉን የጊዜ ሰሌዳ በቅድምያ ተዘጋጅቶ እንዲያዉቁት መደረግ አለበት፡፡
	37. የጤና ተቋማቱ የትዕዛዝ እና የአቅርቦት የጊዜ ሰሌዳዉን መነሻ በማድረግ የመድኃኒት ጥያቄያቸዉን ለቅርንጫፍ ማቅረባቸዉን ክትትል መደረግ አለበት፡፡
	38. ጥያቄዉ በወቅቱ ካልቀረበ አመቺ በሆነ መንገድ ግንኙነት ከጤና ተቋሙ ጋር በመፍጠር ፍላጎቱ መታወቅ አለበት፡፡
	በጥያቄው መሰረት ማቅረብን በተመለከተ፤
	39. ኤጀንሲው የተጠቀሱትን መድኃኒቶች ለማቅረብ በማይችልበት ወቅት ለተጠቃሚዎች ተገቢውን አማራጭ መፍትሄ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	40. ከማዕከል የተመደበውና በፕሮግራም የተደለደለው መድኃኒት ለቅርንጫፎች ከመተላለፉ በፊት በቅድሚያ ቅርንጫፎች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡
	41. ቅርንጫፎች መድኃኒት የሚያከፋፍሏቸው የጤና ተቋማት ዝርዝር መያዝና ሕጋዊነታቸውንም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

	42. የማዕከል መጋዘኖችና ቅርንጫፎች አገልግሎት ለሚሰጧቸው የመንግስት ጤና ተቋማት በሚወጣው የስርጭት ፕሮግራም መሰረት እስከ ተቋማቱ በማጓጓዝ ማስረከብ አለባቸው፡፡
	43. ከሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት የሚቀርቡ የድንገተኛ (emergency) ጥያቀዎች ልዩ ትኩረት አግኝተዉ በአስቸኳይ ምላሽ ማግኘት አለባቸዉ፡፡
	44. ለጤና ተቋማት የሚደረገው የመድኃኒት ክፍፍል የጤና ተቋሙ በሚልከው የመድኃኒት ፍላጎት መሰረት መሆን አለበት፡፡
	45. የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው የደረሱ መድኃኒቶች ለጤና ተቋማት መሰራጨት የለባቸውም፡፡
	46. መድኃኒቶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ ተጠቃሚ ጤና ተቋማት በወቅቱ ለማድረስ የሚያስችል የጤና ተቋማት ምልከታ በየጊዜው የሚዘጋጅበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	47. በምልከታው መሰረት የተጠናከረ የማጓጓዣ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	48. ማንኛዉም አይነት የጥራት ችግር ያለበት መድኃኒት እንዲሰራጭ መደረግ የለበትም፡፡
	49. አንድ መድኃኒት የጥራት ጉድለት እንዳለዉ ወይም ጥራቱ አጠራጣሪ እንደሆነ ሲረጋገጥና በዚህ ምክንያት የሚመለከተዉ ኃላፊ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ ሲሰጥ የመድኃኒቱ ስርጭት እንዲቆም ጥቅም ላይ እንዳይዉልና ተመላሽ እንዲደረግ ፈጣን በሆነ መንገድ መድኃኒቱ ለተሰራጨበት የጤና ተቋም ሁሉ ማስታወቂያ መላክ አለበት፡፡
	50. ከማዕከል መጋዘኖች ወደ ቅርንጫፎች ፤ ከቅርንጫፎች ወደ ማዕከል እና በቅርንጫፎች መካከል ለሚደረጊዉ የመድኃኒቶች ዝዉዉር በጉዞ ወቅት ለሚከሰት አደጋ እንደአስፈላጊነቱ እና አመቺነቱ የመድን ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና ሊሰራጩ የማይገባቸው መድኃኒቶችን ለይቶ ማስቀመጥን በተመለከተ፤
	51. በጥራት ጉድለት እና በብልሽት/በመሰበር ምክንያት እንዳይሰራጩ የተደረጉ መድኃኒቶች ተገቢዉ ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስ አስፈላጊዉ ምዝገባ ተከናዉኖ ተለይተዉ እንዲቀመጡና ዝርዝር መረጃቸው ለመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ግዥ ዳይሬክቶሬት መላክ ይኖርበታል፡፡
	የመድኃኒት አጠቃቀም ግንዛቤን በተመለከተ፤
	52. የመድኃኒት አስተዛዘዝ፣ ዕደላና አጠቃቀም እንዲሁም በመድኃኒት ጎጂ ባህሪያት ዙሪያ የባለሙያ ክህሎት የሚጎለብትበት ተከታታይ ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	53. በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይነት ያለው ትምህርት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	54. የመድኃኒት ፍላጎት ለመተንበይ፣ ብክነትና እጥረትን ለመከላከል የሚስችል የተጠናከረ የመረጃ ኔትዎርክ ሊዘረጋ ይገባል፡፡
የመድኃኒት ክምችት እና ስርጭት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ	**መረጃ ልውውጥና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ**
	55. ኤጀንሲው ከክልሎችና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	56. ኤጀንሲው ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	57. ቅርንጫፎች ለኤጀንሲው በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት የሚያቀርቡበት እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
	58. ኤጀንሲው ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት የሚያቀርብበት እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

አባሪ 3- በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ ጤና ተቋማት ዝርዝር

ተ.ቁ	የጤና ተቋሙ ስም	የሚገኝበት ክልል	መድሃኒት የሚያሰራጭለት የኤጀንሲው ቅርንጫፍ
1.	ጅማ ዩ/ስ/ ሆስፒታል	ኦሮሚያ	ጅማ
2.	ሰርቦ ጤና ጣቢያ		
3.	አጋሮ ጤና ጣቢያ		
4.	ነቀምቴ ሪ/ሆስፒታል		ነቀምቴ
5.	ኡኬ ጤና ጣቢያ		
6.	ጉቴ ጤና ጣቢያ		
7.	ጋምቤላ ሪ/ሆስፒታል	ጋምቤላ	ጅማ
8.	ጋምቤላ ጤና ጣቢያ		
9.	ቦንጋ ጤና ጣቢያ		
10.	ፈለገ-ህይወት ሪ/ሆስፒታል	አማራ	ባህርዳር
11.	መራዊ ጤና ጣቢያ		
12.	ወረታ ጤና ጣቢያ		
13.	ደሴ ሪ/ሆስፒታል		ደሴ
14.	ጢጣ ጤና ጣቢያ		
15.	ኮምቦልቻ ጤና ጣቢያ		
16.	ጳውሎስ ሆስፒታል	አዲስ አበባ	አዲስ አበባ

17.	ጥቁር አንበሳ ሪ/ሆስፒታል		

አባሪ 4- የአሰራር ሥርዓት መግለጫ

2.1 Linear workflow for storage



2.2 Linear workflow for distribution from hub to health facility




No
Yes
Follow up
Submit signed & stamped copies of invoices & delivery note to inventory control clerk
Receive signed & sealed copies of invoices & original receiving voucher
Health facility records variance on the invoice and model before signing on the invoice
Submit signed & stamped invoices & original receiving vouchers; receive inventory control and capacity building information